# ችግራችን ከምን የመነጨ ነው ?

እናት አፍሪካና ልጆቿ በሚል አርእስት በታህሳስ ወር 2004 በተሰፋ መጽሄት ላይ በአቶ መለከት ባየሁ የተደረሰው ግጥም ብዙ ቁም ነገሮችን ያዘለ ጽሁፍ ነው። ደራሲው የአህጉራችንን ችግር ፣ የችግራችንን ምንጭ ያለመረዳትና የኛን ድንብርብር መውጣት ፣ እርስ በርስ መነካከስና መጨራረስ የቱን ያህል ለተረጋጋ ኑሮና ለዕድገታችን እንቅፋት እን ደሆነ በጥሩ ብዕር ቁልጭ አድርጎ አስቀምጧል።

የዚህ ጽሁፍ ዓላማ ደራሲውን ለመተቸት ሳይሆን ፣ በመደገፍ በአገራችን ምድር የተከማቸው ችግር ከምን እንደመነጨና በየጊዜው ስልጣን ላይ በተለያዩ አጋጣሚዎች ቅጥጥ የሚሉ ፣ ችግሮችን ከመፍታት ይልቅ ለምን እያባባሱ እንደሚሄዱና ብሄራዊ ነፃነታችንን አስደፍረው የኢትዮጵያ ህዝቦች ዕድል በኛ ልጆቿ ሳይሆን በውጭ ኃይሎች እንዲወሰን እን ደሚያደርጉ ለማሳየት ነው። የችግሩን ምንጭ መሰረት በአጭር በአጭሩ ለማስቀመጥና አዲሱ ትውልድ ተረድቶት እናት አገሩን ከአደጋ እንዲከላከል ለማሳሰብ ያህል ብቻ ነው።

ላይብኒዝ የሚባለው የ17ኛው ክፍለ ዘመን የማቲማቲክ ፣ የፊዚክስና የፍልስፍና ተመራማሪ አንድ ነገር ካለምንም በቂ ምክንያት ሊከሰት አይችልም ይላል። ድርጊቶች ብቻ ሳይሆኑ ተፈጥሮና የሰው ልጅም ጭምር ስንፈጠር በበቂ ምክንያት ነው። ካለበቂ ምክንያት በዚህች ዓለም ላይ ብቅ ማለት ባልቻልንም ነበር ይላል።

ዛሬ በአገራችን ውስጥ የተከማቸውንና የአገራችንን ህልውና ለማውደም የተቃረበውን ፖለቲካዊም ሆነ የባህልና የህብረተሰብ ተቅዋም መከስከስ ለመረዳት ድሮ እንደምናደርገውና አሁንም እንደምንጽፈው በቀላሉ ለመገንዘብ የምንችል አይመስለኝም። ድሮም ሆነ አሁን ለአገራችን ውስብስብ ሁኔታ በስልጣን የነበሩትና አሁንም ያለው ኃይል ተጠያቂ እንደሆነ አድርገን ነው የምናስቀምጥና ሌላውን ለማሳመን የምንሞክረው። ይህ ዐይነቱ አተናተን ምናልባት የህቁ አንድ አስረኛ ምክንያት ቢሆን ነው። ይህንን ለመገንዘብ ከዚህ አንድ እርምጃ ተራምደን የችግሩን ምንጭ መረዳት ያለብን ይመስለኛል። ከዚህ ስንነሳ የቀድሞዎችን ትተን ፣ አገራችን ውስጥ በሚጥመለመለው ችግርና አገራችንን ለመድፋት በተቃረበው የተወሳሰበ ሁኔታ የዛሬው አገዛዝ ምን ጥቅም ያገኝበታል? ኢትዮጵያ ብትከሰከስና በዘላለማዊ ጦርነት ብተዘፍቅ የሚያገኘው ትርፍ ምንድን ነው ? ለጠቅላላው ህዝብ ይቅርና አገዛዙ በዚህ እርኩስ ተግባሩ ለልጆቹ ምን ዐይነት የታሪክ ቅርስ ጥሎ ይሄዳል? ስልጣን ላይ ቅጥጥ ማለት ታሪክ ለመስራት ወይስ ህዝብን ለማተራመስና ለማብሸቅ ነው? እንደዚህ ዐይነቱ መተረማመስና አገርን ማመሰቃቀል ለምን የታሪካችን ዕጣ ሆነ ?

ከዚህ ቀደም በተለያዩ ጽሀፎቼ ላይ ለማሳየት እንደሞከርኩት ከላይ የሰፈሩትን ጥያቄዎች ለመረዳት በቀጥታ ከምናየው መነሳት የለብንም። ታላላቅ ፈላስፋዎችና የድራማ ሰዎች እንደዚህ ዐይነቱን ችግር ለመረዳትና መፍትሄ ለመስጠት የደረሱበት አንድ ወጤት አለ። ከሶክራተስ ጀምሮ እስከፕላቶንና በኋላም ለተነሱት የጀርመን ክላሲኮች ህብረተሰብአዊ ችግርና ጦርነት እንዲሁም ማቴሪያላዊ ድህነት የጭንቅላት ድህነት ነፀብራቆች ናቸው። በሌላ አነጋገር ዕውነተኛ ዕውቀት ባልተስፋፋበት አገርና የስልጣንን ማማ የጨበጡ ሰዎች በአንዳች ዐይነት ፍልስፍና ላይ በተመሰረተ ዕውቀት የማይመሩ ከሆነና ዕውቀቱም ከሌላቸው ስራቸው ሁሉ ትርምስን መፍጠርና አገርን ወደ መከስከስ ማድረስ ነው። በእነዚህ ተመራማሪዎች አመለካከት ማንኛውም ነገር በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የሚውጠነጠነው በጭንቅላት ውስጥ ነው። እንደ አካባቢ ሁኔታ ፣ እንደ አስተዳደግና እንደቀሰሙት ዕውቀት የሰዎች ጭንቅላት መታነፅ ብቻ ሳይሆን ድርጊታቸውም በዚህ ይወሰናል። በነገራችን ላይ ዛሬ በዐለም ላይ የሚካሄደው ጦርነትና ትርምስ አወቅንና ተማርን ባሉ ሰዎች አማካይነት እንጂ ባልተማሩ ሰዎች አይደለም። ከዚህ የምንረዳው አንድ ሰው የቀሰመው ዕውቀትና መጠን ፣ የአደገበት

አካባቢና ያለፈበት ጠመዝማዛ መንገድ ድርጊቱን ይወስናሉ ማለት ነው። ከዚህ ውጭ ሌላ ተአምር ሊኖር አይችልም።

ነገሩን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ፤ የሰው ጭንቅላት እንዴት እንደተዋቀረ ጠጋ ብለን እንመልከት። ይህንን ለመረዳት የጥንት የግሪክ ፈላስፋዎች የደረሱበት የምርምር ውጤት የሰው ልጅ ጭንቅላት በሶስት ረድፍ የተከፋፈለ ነው። አንደኛው ከውጪ በቀጥታ በምናየው ላይ የሚያተኩር ሲሆን ይህ ክስተታዊ ትዕይንታ (sense perception) ይባላል። ሁለተኛው አርቆ አስተዋይነትን የሚመለከት የጭንቅላት( reason) ክፍል ነው። ሶስተኛው ምሁራዊ ( intellectual)ክፍል ነው። እንደ የአገር ዕድገት ደረጃ የሰዎችም የማሰብ ኃይል ከሶስቱ በአን ዱ ይወሰናል ማለት ነው። ለምሳሌ በታሪክ ውስጥ እንደታየው ጥንታዊ ባህልና የአሰራር ዘዴዎች እንዲሁም ደግሞ ህብረተሰብአዊ አሰላለፍና ንቃተ ህሊና ባልጎለመሱበት አገር ውስጥ የሰዎች አስተሳሰብ በክስተታዊ ትዕይንታ ይሸፈናል። በህብረተሰብ ውስጥ የሚከሰቱ ማንኛውም ችግሮችና ከተፈጥሮ ጋር የተያያዙ አደጋዎች የእግዚአብሄር ቁጣ ተብለው ስለሚወሰዱ በቀላሉ ሊወገዱ የሚችሉ ችግሮች መልስ ሳያገኙ ይቀራሉ። ለምሳሌ ጦርነትና ረሀብ በቀላሉ ሊወገዱ የሚችሉ ነገሮች ሆነው ተፈጥሮአዊ ተደርገው ስለሚወሰዱ ለከፍተኛ ህብረተሰብ መመሰቃቀል ምክንያት ይሆናሉ። በዚህ ላይ አንድ ህዝብ በሀይማኖትና በአጉል አምልኮ አእምሮው ከተጠመደ በህብረተሰብ ውስጥ የሚከሰቱ ችግሮችን የመፍታት ኃይል አይኖረውም። ችግሮች ለምን እንደሚከሰቱ እራሱን ደጋግሞ በመጠየቅ ለችግሩ መፍትሄ መሻት ይሳነዋል። ይህ ዐይነቱ ድክመት በጥንት በግሪክ ስርዓትና በኋላ ደግሞ በአውሮፓ ውስጥ የተንሰራፋና በከፍተኛ የጭንቅላት ስራ ከሞላ ጎደል ሊወገድና የአውሮፓው ህዝብ የሳይንስ ባለቤት ሊሆን በቅቷል። በዚህ ረገድ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ሲወርድ ሲዋረድ የተከማቸ ችግርና ከዚህ ችግር ጋር መኖር እንደ ባህል ተደርጎ በሚወሰድበት አገር ውስጥ መደረግ ያለበት ህዝቡን ከአጉል ዕምነት አላቅቆ አርቆ የማሰብ ኃይሉን በማዳበር የዕወቀት ባለቤት ሆኖ የሳይንስንና የቴክኖሎጂን ቁልፍ እንዲይዝና ወደ ከፍተኛና ጥበብ ወደተሞላበት ህብረተሰብአዊ ክንውን እንዲሸጋገር ማድረግ ነው።

ይህ የግሪኩ ሜታፊዚክሳዊ አቀራረብ በጭንቅላት ላይ በማትኮር ፣ ጭንቅላት በቋንቋ ፣ በሙዚቃ ፣ በፍልስፍናና በተፈጥሮ ሳይንስ ምርምር በመዳበር ስሜታዊነት ከሚያጠቃው የሰውነት ክፍል ላይ የበላይነትን እንዲቀዳጅ ማድረግ ነው። በግሪክ ፈላስፋዎች አመለካከት ፣ አእምሮና(soul) ሰውነት(body) አንድ ላይ የተያያዙ ሲሆኑ ፣ በዕውቀት ማነስ የተነሳ ሰውነት በአእምሮ ላይ የበላይነትን በመቀዳጀት ለጦርነትና ለህብረተሰብአዊ ችግር ዋና ምክንያት ይሆናል። ሰውነት በጦርነት ፣ በስልጣንና በሀብት ስለሚሳብ የሰዎች የማሰብ ኃይልም በዚህ ስለሚሸፈን ድርጊታቸው ሁሉ ሌላውን ማሰቃየትና ህብረተሰብን ማመሰቃቀል ይሆናል። ከዚህ ስንነሳ ዛሬ በአገራችንና በተለያዩ የሶስተኛው ዐለም አገሮች የምናየው ውዝግብ በተወሳሰበ ዕውቀት ካለመዳበር የመነጨና ታሪክን ለመስራት ምን መደረግ እን ዳለበት ግንዛቤ ውስጥ ለማስቀመጥ ካለመቻል የተነሳ ነው። ይህ ማለት ግን የነጭ ዘር ከዚህ ዐይነቱ ክስተታዊ አስተሳሰብ የጸዳና አስተሳሰቡ ሙሉ በሙሉ በአርቆ አስተዋይነት የተገነባ ነው ማለት አይቻልም። ለዚህ ዋናው ምክንያት ላይብኒዝ በ17ኛው ዓ.ም አርቆ እንደተመለከተው የእንግሊዞቹ ክስተታዊ ዕውቀት አይሎ በመውጣቱና ጠቅላላውን የገዢ መደቦችን ጭንቅላት ለመቆጣጠር በመቻሉ ነው። የነ ቡሽም ድንፋታ ከዚህ የስሜታዊነት የበላይነትን ከመቀዳጀት ጋር የተያያዘ ነው። ዛሬ በዓለም ላይ የበላይነትን ሁለንታዊ ለማድረግ የሚደረገው የነጭ ኦሊጋርኪ መደብ ርብርቦሽ ከዚህ የመነጨ ነው። ከነጭ ዘር በስተቀር ሌሎች ቴክኖሎጂን መቀዳጀት የለባቸውም። ሳይንስና ጥበብን ማስፈን የለባቸውም። በዐለም ውስጥ የሚገኙ የጥሬ ሀብቶች ሁሉ የነጭ ሀብት ናቸው። ስለዚህም በቁጥር የሚበልጠውን የጥቁር ህዝብ በተለያዩ ዘዴዎች መቀነስ ፣ ጦርነት መቀስቀስ ፣ እንደ ኤይድስ የመሳሰሉትን በሽታዎች ፈጥሮ ህዝብን ቁራኛ ማድረግና ህብረተሰብአዊ ትርምስ መፍጠር ናቸው። እዚህ ላይ ነው እንግዲህ በጠቅላላው የጥቁር ምሁርና የገዢ መደብ በፍጹም የማይገባቸው። በአንድ በኩል ለስልጣን በመስገብገብ እርስ በርሱ ይበላላል። በሌላ ወገን ደግሞ እንደ አሜሪካ ያለው ፋሽሽታዊና ዘረኛ መንግስት ባጠመደለት ወጥመድ ውስጥ ገብቶ

ይተራመሳል። በተለይም ይኸኛው ለኢትዮጵያዊው ምስኪን ግልጽ ሊሆንለት በፍጹም አልቻለም። በኢትዮጵያውያን አመለካከት አሜሪካ ቅዱስና እንደዚህ ዐይነቱ ተግባር በፍጹም በህልሙ የማይታይ ነው። በአገራችን ውስጥ የተካሄዱትና ዛሬም የሚካሄዱት ውዝግቦች አሜሪካ በፍጹም እጁን አላስገባም። አሜሪካ ኢትዮጵያን አጥብቆ ስለሚወድ የኢትዮጵያን ጥፋት በፍጹም አይመኝም እያሉ ከሱ ጋር በፍቅር የተጠመዱ ሌት ከቀን ለማሳመን የማያደርጉት ሙከራ የለም። እንደዚህ ዐይነቱ መሰወር ከምን የመነጨ ነው?

በአገራችን ምድር ዕውነተኛ በፍልስፍናና በሳይንስ ላይ የተመሰረተ ዕወቀት በፍጹም አልዳበረም። አገራችን የሶስት ሺህ ዐመት ታሪካ አላት ይባል እንጂ የህብረተሰቡን ጭንቅላት የሚከፍቱ ፣ አስተሳሰቡን የሚያጎለምሱ ፣ በሰፊው እንዲያይ የሚያደርጉ የምሁር እንቅስቃሴ በአገራችን ምድር ታይቶ አይታወቅም። በዚህ ላይ የፊዩዳሉ ባህልና ልዩ ልዩ አምልኮዎች ከሀይማኖት ጋር ተጣምረው አስተዳደጋችንን ስለቀረጹት በረጅሙና በወስብስብ ለማሰብ በፍጹም አላስቻለንም። በዘመናዊ ትምህርት መግባት ይህ ሁኔታ በፍጽም መፍትሄ አላገኘም። እንዲያወም በመሳብ አስተሳሰባችንን በማዶልደልም ለአመጽና ለእንቢተኝነት እን ዲሁም ለቂም በቀል በመጋበዝ እንደየካቲቱ ላለው የእርስ በርስ እልቂት ምክንያት ሊሆን በቅቷል። የአገራችንንም ዕድገት ፣ የቤት አሰራር ፣ የከተማዎች ዕቅድ ፣ እንዲሁም ደግሞ በቴክኖሎጂ ወደ ኋላ መቅረታችንን ጠጋ ብለን ስንመረምር መልሱ ጭንቅላታችን በዕውነተኛ ዕውቀት አለመዳበሩ መሆኑን መገንዘቡ ከባድ አይሆንም። ይህ ጉዳይ ከሰላሳና ከአርባ ዐመት በኋላም መፍትሄ ያገኝ አይመስልም። እንዲያውም ይባስ ብሎ የኋሊት ጉዞ እያደረግን ነው። ባለፉት አስራ አራት ዓመታት የሚሰጡትን ትንተናዎች ስንመለከት አንድ ሜትር እንኳ ፈቀቅ እንዳላልን ማረጋገጥ እንችላለን። የራሳችንን ታሪክና ድርጊታችንን በሳይን ስ መነጽር ለመመርመር የተሳነን እንመስላለን። ነገሮችን ከወዲህና ከወዲያ በመለቃቀም ገጣጥምን በመጻፍ ከመንደፋደፍ በስተቀር ዕውነተኛ ሳይንሳዊ ትንተና በመስጠት ወደ ሀቁ ለማምራት ሙከራ ስናደርግ አንገኝም። አንዳንዶች ሙከራ ሲያደርጉ እነሱን እየተከታተልን ለማውደም እንታገላለን። ይህ ፊውዳላዊ አስተሳሰባችን ጠላትን ከወዳጅ ለመለየት በፍጽም አላስቻለንም። አገራችን እንዴት አድርጋ በተቀነባበረ ሴራ ከውስጥና ከውጭ እን ደምትቦረቦርና ለከፍተኛ አደጋ እንደተጋለጠች በፍጹም ልንገነዘብ አልቻልንም። ጭንቅላታችን ስለታወረ በአይናችን ስር የሚሽከረከረውን ሴራ ጠጋ ብሎ መመልከት ተስኖናል። በአጭሩ ድርጊታችን ሁሉ እንኳን የሶስት ሺህ ዐመት ታሪክ ያለን የሚያሰኝ ቀርቶ የመቶ ዐመት ታሪክ ያለን አንመስልም። ጭንቅላታችን የተበታተነና ግራ የገባን ነን። ምን እንደምንሰራና ምን እንደምንፈልግ የምናውቅ አይመስለም። ወረት ያጠቃናል። አብሮ ተባብሮ መስራትና መደማመጥ ባህላችን አይደለም። የምናስበውንና የምንፈልገውን አውጥተን መናገር በፍጹም አንችልም። በራሳችን ላይ ዕምነት የለንም። ይህች ዐለም ምን ያህል የተወሳሰበችና አገርን ለማዳንና ለመገንባት እንደዚሁ ትልቅ የጭንቅላት ትግል መካሄድ እንዳለበት በፍጹም የተረዳን አይደለንም። በአንፃሩ ቻይናዎችና ሌሎች የኤሺያ አገሮች የሚሰሩትን ተዓምር ጠጋ ብሎ መመልከት ያስፈልጋል። በፍጹም በራቸውን ለምዕራብ ከፍተው አይሰጡም። እያንዳን ዱን የነጭ እንቅስቃሴ ይከታተላሉ። በዚያ መጠን ደግሞ ቴክኖሎጂዎች አስገድዶ ማግኘት ብቻ ሳይሆን ይሰርቃሉ። ብዙዎቹ እዚህ ለትምህርት ሲመጡ 1ኛ) የሚማሩት ትምህርት ለአገራቸው ዕድገት የሚጠቅም ነው ፤ 2ኛ) በደንብ ተምረው ይሄዳሉ ፤ መጽሀፎች ገልብጠው ወይም ኮፒ አድርገው ይወስዳሉ። 3ኛ) የትምህርታቸው ዐይነት የተሰበጣጠረ ነው። ሙዚቃ ፣ ሌትሬቸር ፣ ቋንቋ ፣ የተፈጥሮ ሳይንስና የቴክኖሎጂ ትምህርቶችን ተምረው ድምጻቸውን ሳያሰሙና የነጭ መሳሪያ ሳይሆኑ ወደ አገራቸው ይመለሳሉ። እኛ ግን ለዚህ የተካንን አይደለንም።እዚህ ላይ ነው እንደግዲህ በእኛ በአፍሪካውያንና በኤሺያ ህዝብ መሀከል ያለው ልዩነት።እኛ በየዐመቱ በልመናችን እርስ በራሳችን እየተብላላን እንኖራለን ።እየታዘነልንና በኛ ስም ገንዘብ እየተለመነልን እንደዚሁ በትዝታ ዐለም እንኖራለን። የታሪክ ውርደት የተከናነብን። በፍጹም የማይገባን።

ከዚህ ስንነሳ የዛሬውን አገዛዝ ድርጊትም ሆነ እሱን እንቃወማለን የሚሉትን ኃይሎች ሁኔታ ስንመለከት የተምታታ ሁኔታ እንመለከታለን። በመጀመሪያ የዛሬው አገዛዝ

የሚሰራቸው ስራዎች ሁሉ ልክ እንደ ሺህ ዐመት የሚቆይ መስሎት ነው አንዱን ከአንዱ ጋር በማምታታት ስልጣን ላይ ለመቆየት የሚንደፋደፈው። በዚህ የተምታታ ድርጊቱ ቢቀር እንኳ ለልጆቹ እፎይ ብለው እንዲኖሩ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት አልቻለም። የቆሰቆሰው የክልል ፖለቲካ ፣ በር ክፍቶ የሰጠው የሀይማኖት መፈልፈል ፣ የስለላ ድርጅት መስፋፋት ፣ እነዚህ ሁሉ አገሪቱን ትርምስ ውስጥ እንደሚከቷት በፍጹም አልታየውም። በዚህ ላይ ደግሞ በዚህም በዚያም ብሎ ሀብት በማግሰበሰበስ ብቸኛው ሆኖ በመቅረብ የህብረተሰቡን ዕድል ብቻውን ወሳኝ ሆኗል። እነዚህ የተከማቹ ነገሮች ሁሉ አጥፍቶ መጥፋትን እንደሚያስከትሉ በፍጹም ሊገነዘብ አልቻለም። እዚህ ላይ ነው እንግዲህ ራሳችንን መጠየቅ ያለብን። እን ደዚህ አስራ አራት ዓመት ያህል የተከማቸ ችግር እያለ አገዛዙ ሁኔታውን ለምን የባሰ እያግማማ ይሄዳል? ለምንስ በዚህ በተግማማ ሁኔታ ላይ በአንድ በኩል እራሱን ያጠናክራል ? በሌላ ወገን ደግሞ ለምን የውስጥ ለውስጥ አፈናውንና ግድያውን ያካሄዳል? ችግሮች እን ደዚያ አፍጠው አግጠው ለእነሱ ሳይንሳዊ መልስ ከመፈለግና ምክር ከመጠየቅ ይልቅ በእልክ ተግባሩ የወደፊት ሽምጥጫውን ለምን ተያያዘው? ከዚህ ስንነሳ ይህ ጉዳይ የኛው አገር ችግር ብቻ ሳይሆን የብዙ አፍሪካ አገር መሪዎችም ችግር መሆኑን መገንዘብ ያሻል። የሁኔታዎች ደረጃና ሂደት ቢለያይም በይዘትም ሆነ በድርጊት አንድ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል። ዞረን ዞረን ለዚህ ጥያቄ የምናገኘው መልስ ሜታፊዚክሳዊ ነው። ማለትም የመሪዎች ጭንቅላት ከራስ በአሻገር ማሰብ የማይችል ፣ ኃላፊነት የጎደለው ፣ ህብረተሰብአዊ ኃላፊነትን የማይረዳ ፣ በራሱ ዙሪያ የሚሽከረከርና ህዝብን የሚንቅ አገዛዝ እዚህና እዚያ እንደሰፈነ መረዳት ይቻላል። ይህ በአገዛዙ አካባቢ ያለውን ድንቁርናና ወደፊት ለማየት ያለመቻል ሁኔታን ሲያመለክት በሌላ ወገን ደግሞ በተቀዋሚ ዘንድ ያለውን የፖለቲካ ትርምስ መመልከቱ እጅግ አስፈላጊ ነው። ተቃዋሚው ኃይል የዛሬው አገዛዝ እንዴት እን ደተነሳና እንደሚንቀሳቀስ ፣ እንዲሁም ደግሞ ከውጭ ኃይሎች ጋር ያለውን ትስስር በፍጹም ሊገነዘበው አልቻለም። በፊዩዳል አርቆ አስተዋይነት በመወጠሩ የውጭ ኃይሎች አገራችንን ብትንትኗን ለማውጣት የሚያደርጉትን ሽረባ በፍጹም ሊገነዘብ አልቻለም። የጭንቅላት መታወሩ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ በዐይኑ ዘንድ የሚሽከረከሩ ነገሮችን ለማየት ፣ ለመቃወምና ለእነሱ ሳይንሳዊ መፍትሄ ለመስጠት የሚችል አይደለም። ዋናው ነገር የዛሬውን አገዛዝ በዚህም በዚያም ብሎ መጣል ነው። ከዚያ በኋላ ዐይን ፍጥጥ እያደረጉ ወደ አሜሪካን በር ለማንኳኳት መጓዝ ነው። እንደነ ናይጀሪያውና ኬኒያ ዐይነት ትርምስ ውስጥ እንገባለን ማለት ነው። ከዚህ ውጭ ነፃ አውጪ ነን የሚሉና ምንም ዕውቀት የሌላቸው ፣ ጥላቻን መርሆዋቸው ያደረጉ እጅግ አደገኛ ኃይሎች አሉ። እነዚህ እኛም አገር ማስተዳደር የሚሳነን አይደለምና ባለተራ ነን ባዮች ናቸው። የወደፊቱ የኢትዮጵያ ዕጣ ደንቆሮዎች የሚጨፍሩባት የጦር አውድማ የምትሆን አገር ናት ማለት ነው። እነዚህን ድንብርብራቸው የወጣ ኃይሎችን ለመግታት ብዙ ስራ መስራት ያስፈልጋል ማለት ነው። ያልታደለች አገር ! ያልታደለ ህዝብ !

በአጠቃላይ ወደ አቶ መለከት ባየሁ ግጥም ጋ ልምጣና አፍሪካ የነጭ አሊጋርኪ መደብ በጠመደው ወጥመድ ውስጥ ገብታ ስትሰቃይ ከአራት መቶ ዐመታት በላይ ሊሆናት ነው። በመጀመሪያ በ15ኘው ክፍለ ዘመን እንደከብት እየተጓዘ የሄደው ከሰላሳ እስከ 90 ሚሊዮን የሚጠጋ ጥቁር አፍሪካዊ በእየአገሩ አሉታዊ ተጽዕኖችን አሳድሯል። አንጥረኛ ፣ ነጋዴ ፣ አራሽ ፣ ጥበበኛና የባህል መድህኒት ቀማሚዎች እየተነቀሉ በመወሰዳቸው የቀረው ሽማግሌና ህጻናት ብቻ ነው። ስርዓቱ እንዳለ ሲፈረስ የቀረው ኃይል የስራ ክፍፍልን ለማዳበር ሀ ብሎ መጀመር ነበረበት። አንድ አገር አንድ ጊዜ ከወደመ ፣ በተለይም ሊሰራ የሚችል ከሌለ መልሶ ለመገንባት በፍጹም አይቻልም። ይህ ሁኔታ በዘመነ ቅኝ አገዛዝ ባሰበት። በአዲሱ የቅኝ አገዛዝ አስተዳደር አፍሪካውያን የሰለጠኑበትን ሙያ እየተው ለነጭ በማረስ የአውሮፓ ሀብት እንዲዳብር ፣የኢንዱስትሪ ዕድገት እንዲበለጸግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አደረጉ። ወደ ውስጥ ግን ከተማዎች ፣ ኢንዱስትሪዎችና ልዩ ልዩ የመገናኛ መስመሮች እን ዳይዘረጉና ህዝቡ እርስ በርስ እንዳይተሳሰርና ብሄራዊ ስሜት እንዳይኖረው ተንኮላቸውን ሸረቡ። ይህ ኋላ ለተከሰተው በጎሳና በሀይማኖት መከፋፈል ፣ ወይም ደግሞ ቀድሞ የነበረው ልዩነት እንዲሰፋ በማድረግ ዛሬ ለምናየው ትርምስ መሰረት ጣለ። እንደሚታወቀው እስከ

ባርያ ንግድና ቅኝ ግዛት አስተዳደር ከመምጣቱ በፊት ብዙ የአፍሪካ አገሮች ፣ በተለይም እንደ ጋና ፣ ናይጄሪያ ፣ ቤኒንና ማሊ(ቲምቡክቱ) የስራ ክፍፍልና ንግድ የዳበረባቸው አገሮችና ከተማዎች እንደነበሩ የተረጋገጠ ነው።

ከቅኝ ግዛት አስተዳደር ነፃ መውጣት በኋላ አልሸሹም ዞር እንደሚባለው አነጋገር በየቦታው የተቋቋሙት አገዛዞች የየህብረተሰቦቻቸውን ጥቅም የሚያስከብሩና ለዕድገት ተቆርቋሪ ሊሆኑ የሚችሉ ኃይሎች አልሆኑም። አንዳንድ የተገለጸላቸው ብቅ ሲሉና ለውጥ ለማድረግ ሲሞክሩ እነሱን ማሳደድ ፣ መግደልና ማሰር ሌላው ሙያ ሆነ። በስድሳኛውና በሰባኛው ዓመታት የተካሄዱትንና የተሞከሩትን የመንግስት ግልበጣ ሙከራዎች ጠጋ ብሎ መመልከት ያስፈልጋል። በዚህ ሁኔታና ብዞዎችም መንግስታት ከውጭ ኃይሎች ጋር በጥቅም በመለላሳቸው መሰራት ያለባቸውን ተግባሮች ማካሄድ ተሳናቸው። መንግስታቱ የየህዝቦቻቸው አለኝታ ከመሆን ይልቅ ጨቋኝ ሆኑ። ህብረተሰብአዊ ሀብትን ካማዳበር ይልቅ አባካኝ በመሆን አፍሪካን አራቆቷት። ይህ ሁኔታ የባሰ ትርምስን ፣ በሀይማኖትና በጎሳ መከፋፈልን ፣ የአስተዳደር ልቅነትን ፣ ሰርዓተ-አልባነት መስፋፋትን ፣ ማጅራት መችነትን እንዲሁም ልዩ ልዩ ጋጠ ወጥ ስራዎች እንዲስፋፉ በር ከፈተ። በአጭሩ በብዙ የአፍረካ አገሮች ውስጥ ስርዓት ያለው አስተዳደር የለም። ወደፊትም የሚመጣ አይምስልም። ይህ ሁኔታ ብዙ የአፍሪካ አገሮችን እያተራመሰ እያለ በእንግሊዝና በአሜሪካን ቅንብር የሚካሄደው ሴራ ዐይን ያወጣ ሆኗል። አሜሪካንና ጠቅላላው ሰለጠንኩኝ የሚለው ምዕራብ አውሮፓ እን ደነሞብቱ የመሳሰሉትን አረመኔዎች ለብዙ ዐመታት ከደገፈና እንደሎሚ መጥጦ ከጣለ በኋላ ዛሬ በኮንጎ ህዝብ ላይ ቀጥተኛ ወረራ እያካሄደ ነው። በኮንጎ ምድር በሩዋንዳና በዩጋንዳ አማካይነት የሚካሄደው ጦርነት በቀጥታ በአሜሪካንና በእንግሊዝ የሚደገፍ ነው። በአንድ በኩል የኮንጎ ህዝብ እየደማ ሀብቱ መዘረፍ አለበት። በሌላ በኩል ደግሞ በምንም ዐይነት ህዝቡ የተደላደለ ስርዓት መመስረት የለበትም። እንደዚሁ በአንጎላና በሞዛምቢክ ከ20 ዐመታት በላይ በተካሄደው ጦርነት ሲአይኤና አንዳንድ የምዕራብ መንግስታት ለሳሚምቢና ለፍሬናሞ የገንዘብና የመሳሪያ ዕርዳታ በመስጠት ለብዙ ሺህ ህዝብ እልቂት ተጠያቂ ናቸው። የጦርነቱ ውጤት እስከዛሬ ድረስ አፍጦ ይታያል።ይህ ነው ስለጠንኩ ባይ ነኝ የሚለው የነጭ ዘር ፍልስፍና። እንደዚሁ በሴራሊዮንና በላይቤሪያ እስከቅርብ ገዜ ድረስ የተካሄደው ጦርነት የአሜሪካንና የእንግሊዝ እጅ እንዳለበት ይታወቃል። በአይቮሪ ኮስት የሚካሄደው የእርስ በርስ ግጭት ፈረንሳይ የምታተራምሰው። ወደኛ አገርም ስንመጣ ለሱማሌ መንግስት መሳሪያ በማቀበል አገራችን ተወጥራ እንደነበር ግልጽ ነው። በአብዮቱም ወቅት እንደዚሁ ምስኪን ኢትዮጵያውያን በሲአይኤ እየተመከሩና እየተደገፉ የማይገባ እልቂት እንዳካሄዱና ብዙ ወጣትና ምሁር እንዳስጨረሱ ግልጽ ነው። እዚህ ላይ ቂም በቀል ለመወጣት ሳይሆን ምን ያህል ደንቆሮዎች እንደሆንና አሁንም በሲአይኤ አቀነባባሪነት የምዕራቡ ዐለም በኛ ላይ የተቀነባበረ ሴራ እንደሚያካሄድብን ለመግለጽ ብቻ ነው። ነገሩ ውስብስብና ከኛ አቅምና ዕውቀት በላይ በጥቁር ህዝብ ላይ ምን ያህል ግፍ እንደሚካሄድ ለመጠቆም ነው። በኤርትራና በኤትዮጵያ መሀከል የተካሄደው ጦርነትና አሁንም አፍጦ ያለው በአሜሪካኖች ገፋፊነት እንደሆነ ግልጽ ነው። ኢትዮጵያ ተደላድላ መኖር የለባትም። በዚህ ላይ ደግሞ በኦሮሞ እንቅስቃሴ የሚካሄደው የነፃነት ትግል በተዘዋዋሪ በሲአይኤ ፋይናንስ የሚደረግ ነው። የኦሮሞ ነፃ አውጭ ድርጅት ነኝ ባዩ በሱዳን የነፃነት እንቅስቃሴ አማካይነት የመሳሪያና የገንዘብ ድጋፍ ያገኛል። ጆን ጋራንጅ ደግሞ በሲአይኤ በዐመት $ 10 ሚሊዮን ድጋፍ ያገኛል። ሌሎች የአሜሪካን ወግ አጥባቂ ድርጆቶች ጦርነቱን ፋይናንስ ያደርጋሉ። ይህንን ሁኔታ የኢህአዴግ መንግስት በደንብ ያውቀዋል። እንገዲህ ሁኔታው እን ደዚህ ምስቅልቅሉ የወጣ ነው። እኛ አፍሪካውያን እንደከብት የምንነዳ ነን ማለት ነው። ይህንን ትርምስ ሁኔታ በፍጹም የተገነዘብን አይምስለኝም።

በእኛ በኩል የሁኔታውን አደገኛነት ተገንዝበን ከዛሬው ታጥቀን መነሳት አለብን። ከተዝረከረከ ስራ ወደ ሳይንሳዊ ተግባር በማምራት ለመጪው ትውልድ የታሪክ መሰረት ጥለን ማለፍ መቻል አለብን። በዚህም በዚያም ብሎ ለመሸሽ የሚደረገው ሙከራ መቅረት

**አለበት። ከቻይናዎች ብዙ መማር አለብን። ከራሳችን ይልቅ ህዝባችንና አገራችንን በማስቀደም ታሪክን ለመስራት ቆርጠን መነሳት አለብን። ለዚህ ደግሞ በፍልስፍናና በሳይንስ ላይ የተመረኮዘ ትግል ማካሄድ አለብን። ከዚህ በተረፈ ትግላችን ተጨባጭ እንዲሆን ከተፈለገ ፣ 1ኛ) እዚህ ሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ስልጣኔ አጋዥ ኢንስቲቱት ማቋቋም አለብን። ካለ ኢኒስቲቱት ወደ ፊት ብዙ እርምጃ ማድረግ በፍጹም አንችልም። 2ኛ) ለወጣቱ ትውልድ የዕደ ጥበብ ሙያ ማሰልጠኛ ጣቢያ ማቋቋም አለብን። ይህንን እዚህ ጀርመን የምንኖር ኢትዮጵያውያን ገንዘብ በመሰብሰብ ተግባራዊ ልናደርግ እንችላለን። እኛ ከጀመርን በዐለም ላይ ተበታትነው የሚገኙ ኢትዮጵያውያን እንዲተባበሩን ጥሪ ማድረግ እን ችላለን።እንግዲህ ለአገራችን የምንቆጭ ከሆነ በስሜት ብቻ ሳይሆን ወደ ተግባርም ለማምራት ከዛሬው ቆርጠን መነሳት አለብን። ካለበለዚያ መፎከርና መጻፍ ወደ ዳቦ እን ደማይመነዘርና ታሪክ እንደማያሰራ ተገንዝብን እጃችንን አጣጥፈን ብንቀመጥ ይሻላል። መልሱን እጠባበቃለሁ።**

**ፈቃዱ በቀለ**